# ኢትዮሚዲያ

ርእሰ አንቀፅ

# የቅጥፈት ጌታዎች

(ትርጉም ጠጅቱ ዲባባ)

ማባሪያ የለሽ ውሸታሞች አሁንም እንደገና ቀጥለዋል። የመለስ የዉሸት ትረኢት በሙሉ ኃይሉ የውሸት ቋጠሮዎችን እያጠራቀመ ነው። በዚህ ሳምንት የመለስ የውሸት ኩባንያ እንደነገረን ለሱዳን መሬት አሳልፎ አለመሰጠቱን በጋዜጣ መግለጫዉ ቀባጠረ። እንደሚሉን ሁሉም የስማ በለው ወሬ ብቻ ነው አሉ። የአይን ምስክሮች ዘገባዎች ተካዱ። የሱዳን መንግስት መግለጫ ተሸመጠጠ። የተፈናቀሉ የሀገሩ የምጣኔ ሀብት ባለቤቶች፣ በልማት ላይ የተሰማሩ የዉጭ ሀገር ዜጎች እንዲሁም የአካባቢው ገበሬዎች የችግሩ ሰለባ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን እስከነመኖራቸ ተስተባበለ። ከአካባቢው የተገኙት የፕሬስ ዘገባዎች የአሜሪካ ድምፅና የጀርመን ሬዲዮ ቃለ መጠየቆች በሙሉ ያልተረጋገጡ ወሬዎች ተባሉ።

እርግጠኛ ነን አንዳንድ አንባቢያን የመለስንና ተባባሪዎቹን ዉሸት ሲያነቡ እንደሚደነግጡ። ግምታቸው በአንድ ሳምንት ውስጥ 7 ቀናት አሉ። ዝናብ ከደመና ይመጣል። ፀሃይ በምስራቅ ትወጣለች።የሚለውን እውነታ የተከተለ በመሆኑ ሊሆን ይችላል የድንጋጤአቸው መንስኤ።ለማንኛውም ይህ ግን ማለት የፈለግነዉን ጉዳይ እንዳያስተን። የእኛ ድርሻ ኃላፊነት የጎዳውን የመለስና ኩባንያውን የውሸት መጠን ስፋት ለማመልከትና ሀቅን መካዱን ለማሳየት ብቻ ሳይሆን አስደንጋጭ ክብረቢስ ሀሳባቸው በመቀልድ ሊያስትላልፉብን መጣራቸውን ጭምር ማስመልከት ነው። በእውነት ለመናገር ማንኛውም የሰው ልጅ ይህን ያህል የሞራልና የስነ ምግባር ዝቅተኝነት ደረጃ ይወርዳል ብሎ ለመናገር ይከብዳል።

ባለፉት ጥቂት ሳምንታት መለሰና መሳዮቹ እጅግ ዲሞክራሲ የተሞላበት አራት ሚሊዩን ተወዳዳሪዎች የተሳተፉበት ምርጫ ማድረጋቸውን ነግረዉናል። ይህም እናሳምናቸው ምርጫ መሆኑን አግኝተነዋል። በሚሊዩን ብር የሚገመት ወርቅ ከባንክ ማንም ሳያየው በጠራራ ፀሐይ ቀን ለቀን መወሰዱን ነግረዉናል። የመገረም ሳቅ ሳቅን።ራሳችንንም በትዝብት ነቀነቅን፣ አሁን የያዝነዉ ወቅት የመጨራሻዉ የአመራር ዘመኑ ማክተሚያ መሆኑን መለስ ነግሮናል። በመደነቅና በመሬትም ላይ ተንከባለን ሳቅን፣ አዲሰ የስራ ዘርፍ አንዱ በአንዱ መስመር የቆመ አስቂኝ የኩምክና ተገባር ሊጀምር ይሆናል በማለት ተስፋ እናድርጋልን። እነዚህ በቅጥፈት የሰለጠኑ ዉሸታሞች ትልቅና ትንሽ ውሸት ይነግሩናል። ሲነግሩንም በተደጋጋሚ እንዳይረሳን አድርገው ነው። እነዚህ የሀሰት ስልቻዎች የ1997ን

ምርጫ ማሸነፋቸዉን ነግረዉናል፣ በኢትዮጵያ የፓለቲካ እስረኞች የሉም አሉን፣ የራሳቸዉ የአጣሪ ኮምሽን በአነስተኛ ጊዜ አጣርቶ ሰላሳ ሺህ የፓለቲካ እስረኞች እንዳሉ መዝግቧል። የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህንን አህዝ ከፍ በማድረግ ወደ ሀምሳ ሺሕ አሳድጎታል።በመቀጠል ደግሞ ያልነበሩ አስር ሺሕ የፓለቲካ እስርኞች ከእስር እንደለቀቁ መለስና አሳላፊዎቹ አስታወቁ፣ ስለ ለቀቋቸው እስረኞችም የኛን ምስጋና ፈልጋዋል። በሀገሪቱ ሊነገር የሚችል የሰዉ መብት ረገጣም እንደሌለም ተናግራዋል። ይህንንም የሰዉ መብት መገፈፍን በትክክል ማረጋገጫ ልናቀረብላቸዉ ስንል ወደ ኃሊት አፈገፈጉ። በዲፕሎማሲያዊ ሽፋን በድጋሚ እንዳይሰማ ለማድረግ ሞከረ። ለቡሽ አስትዳደርም ቀንዳምና አይን ያለው አዉሮ ጅሀድ ሱማሊያን ስለያዘ፣ መዋጋት አልብን በማለት አስታውቁት።በመቀጠልም ከሱማሊያም በሁለት ሳምንት ለቀዉ እንደሚወጡ ቃል ገቡ። ይኸው ሁለት አመት ሆኗቸዋል። በአሁኑ ወቅት ራሳቸውንም በሱማሊያ የአሽዋ ድቡሽት ጠልቀዉ አግኝተውታል። አሁን ደግሞ የኢትዮጵያን ምድር ለሱዳን ያለመሸጣቸውን ወይም በነጻ ያለመስጠታቸውን እንድናምናቸው ይነግሩናል። እባካችሁ እረፍት ስጡን (አታታሉን)። አንባቢወቻችንን ስለአባባላችን ይቅርታ እንጠይቃልን። ነገር ግን ለምን በጣም ይዋሻሉ? ለምንስ ብዙ ድሮችን ያጠነጥናሉ? ወይም ይጠብቃሉ ያለያም በቱቻ ገመድ ማሰር ይሄዳሉ? ለአንባቢዎቻችን ለነዚህ ጥያቄዎች ብዙ ምርጫዎችን ስጥተናል።

**እውነትን መያዝ ስለሚያቅታችዉ ይዋሻሉ**

ከመለስ አገዛዝ ብዙ ውሽቶችን ሰምተናል “እኛ ከበስተጀርባ በየጊዜው ባሉ ችግሮች በሚገለባበጡ ታሪኮች እንደጠፋን ይሰማናል። ምክንያቱም ሁሉ ነገር በድብቅና በግርዶሽ ተሽፍኖ ሰማይን አጋጦ በማየት መፍገግ ሆኖብናል።” ሊያምኑበትና ሊቀበሉት ያልቻሉት ለዝርዝር የሚሰለቹ እዉነቶች አሉ። ከኒዚህም ጥቂቶቹን ለምጥቀስ ስልጣን ያዙ፣ በስልጣን ላይም ተዘፈዘፉ፣በሰዉ ፈቃድ ሳይሆን በመሳሪያ ኃይል ስልጣን ላይ ተቆናጠው አንለቅም አሉ። የአባገነን (dictatorship) አገዛዝና የሕዝብ ፈቃድ አገዛዝ( democracy) አንድ አይደሉም። ሁለቱም በእንግሊዝኛዉ አፃፃፍ በ ”ዲ’ ቢጀምሩም ምርጫን መሰረቅ ማለት በምረጫ ማሸነፍ ማለት አይደለም። የህዝብ አገዛዝ ( democracy ) የሌብነት አገዛዝ ማለት አይደለም። በመቶ የሚቆጠሩ ያልታጠቁ ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ገዳዩችን ማሰማራት የኃይል እርምጃ መውሰድ የሰዉን መብት መጠብቅ አይደለም። ተቃዋሚዎችን ካለምንም የሕግ ድንብ ማሰቃየት በትክክል በሕግ ስርአት ዳኝነት በስጠትና ማስተዳዳር ማለት አይደለም።

## ይዋሻሉ፣ ምክንያቱም ተወራራሽ የውሸት በሽታ አለባቸዉና።

ይዋሻሉ ምክንያቱም ውሸት በሚያስደስታቸው ሰወች በሽታ የተለከፉ ናቸውና። ተወራራሽ የውሸት በሽታ በሚባለው የበሽታ አይነት ስለተለከፉ አሁንም ይዋሻሉ። በዚህ አይነት ሕመም የተያዙ ሰዎች በተፈጥሮ በውሸታምነታቸው ይታወቃሉ። በተከታታይ ይዋሻሉ የተናገሩት ውሸትም በውነት ላይ የተመሰረተ ነው በማለት ለሕዝቡ በሚያቀርቡት ንግግር ያምናሉ፡ ውሸታቸውን ለማሳመር ይተርካሉ፣
በጽሑፍም ሆነ በንግግር የአምሮ ፈጠራ ዝብርቅርቅነት/ያልተያያዘ ታሪክ ያቀርባሉ።

ስለውሸታቸው ሲጠየቁ የፈጠሩትን የውሸት ታሪክ በሌላ ላይ ለማላካክና ለመካድ ይጥራሉ። የንግግር ስልት የአምሮ ጠበብት ሲያስረዱ የዚህ አይነት በሽተኞች ያለማቋረጥ ይዋሻሉ። ውሸታቸውንም በተቋም ሆነ በግል በብዛት መቆጣጠር አይችሉም በማለት ይገልጻሉ፡ አገዛዙም ለሱዳን መሬት መስጠቱንት አስመልክቶ በማስረጃ የቀረበበትን ሀቅ በተጠናወታቸው የውሸት በሽታ አስተባበሉ።

## በመዋሸት የሚኖርበት ምድር ላይ ስላሉ ይዋሻሉ

አጉል ዝናን የሚያበስረው አስማታዊ ድራጎን (አስፈሪው ፍጡር) በውሸት ምድር ላይ በአጭር ባጭሩ የሚትነፍስ ይመስላል። ድራጎኑ ሳንዲ የምትባል አንዲት ትንሽ ልጅ ይውስዳል። ሳንዲ በመኖሪያ ቤቷ የገጠማትን ችግር ለማምልጥ ወደውሸት ምድር ለመሄድ በጣም ከሚገመተው በላይ በመዋሸት ላይ እንዳለች ፣የታወቀውን ውሸት ነጋሪ ልጅ ፒኖኪዬን ታገኘዋለች። ልጁ የማሳሳቻ ማስጠንቀቂያ ይናገራል እናም ቅንነት እንደወንጀል ተቆጥሮ በክስ ላይ ነው አላት። ሳንዲም ለድራጎኑ ማንም አይቷት የማያውቅ ወይን ጠጅ መልክ ያላት ላም እንደዚሁም ማንም አይቶት የማያውቀው ሮዝ ቀለም ያለው ዝሆን አንዳንዶች አልፎ አልፎ እንዳዬ በዚህም ወቅት ኪለሮይ ከዚያ ነበር አለች። አቧራማ በሆነው የኦጋዴን መሬት ላይ፡ ስምንት ሺህ ጠንካራ አዉሬ አይንና ቀንድ ያለዉ የአልካይዳ ጂሃድ ጦር ኢትዮጵያን ለመውረር ተነስቷል ተብሎ ተነገርን። ይኸዉም ቀንዳማዉ ጂሃድ መጣ ሄደ። እንደ ወይን ጠጁ ላም ወይም እንደ ሮዙ ዝሆን ብዙ ያልተጨበጡ ነገሮች ሆነው ቀርበዋል።

## ደደቦች ናቸዉ ብለው ስለሚያስቡን ይዋሻሉ።

ምን ያህል ደደባች ናቸው ብለው ያስቡናል? እንደምገምተው በጣም ደደብ በተከታታይ ከአንዱ ውሸት ወደሌላ ውሸት በድፈረት እየነገሩን የመሄዳቸውን ሁኔታ እንዴት ለመግለጽ ይቻላል? ለምን ደደቦች ናቸው ብለው ስለሚያምኑ ባለስልጣንኑ

አትከራከር በሚል አስተሳሰብ፣ እኛ ብለናል ስለዚህ እውነት ነው፣ እዉነት እስከሆነም ድረስ የእዉነት መረጋገጫ አያስፈልገውም፣ ምክንያቱም የእኛ አባባል እውነት ነውና፡ በሚሊዩን ብር የሚገመት ወርቅ ከባንክ መወሰድ የማይታመን ታሪክ እንዴትስ መጣ? ምናልባት እንዲያው እንደሚያስቡን ደደባች አይደለንም። በሌላ በኩል ልንሆንም፡ አንችልም። ፎራስት ጋም የተባለዉ እንዳስቀመጠዉ "ደደብነት ደደብ እንደሚስራው የሚያደግ" ነው።

## በእውንትና በውሸት መካከል ያለውን ልዩነት ስላማያዉቁ ይዋሻሉ።

አብርሃም ማስሎ እንዳለዉ "ያለህ መሳሪያ መዶሻ ብቻ ቢሆን፡ ችግር ሁሉ ሚስማርን ማመሳሰል ይጀምራል" የምታገኘው (የምትሰማው) ሁሉ ውሸት ሲሆን ወዲያው ማንኛውም፡ እውነት ውሸት ይመስላል፡ ልክ እንደሳንዲ በውሸት እንዲሚኖርበት ምድር ለአንዳዶች ውሸትን ከእዉነት ለይቶ ለማወቅ ያለመቻላቸው ሊሆን ይችላል ስለሆነም ስለ ሮዙ ዝሆን፣ ስለ ወይን ጠጇ ላም፣ እምኑልን ምርጫን፣ ቀንዳሙ ጅሃድና በጠፈር ያሉ ከተሞችን ለዘይት መጠቀም መሸጥን ( ወይም በለውጥ) መሰጥጠቱን መካድ ታሪክ ነገሩን ።

## የትልቅ ውሸት ኃይል ስለሚገባቸዉ ይዋሻሉ

ካለምንም ጥርጥር የውሸት ጌቶች ናቸው። ያለፈው ክፍለ ዘመን የመጨረሻው ታላቅ ውሸታም አዶልፍ ሂትለር እንዳስተማረው በትልቅ ሲዋሽ የበለጠ ይታመናል ይላል። ትልቅ ውሸት በተደጋጋሚ ፊት ለፊትና በራስ በመተማመንና በስልጣን ሲደገፍ ማንኛውም ሰው የተነገረውን ያምናል። ላለፉት አስራ ሰባት አመታት በተደጋጋሚና በቀጥታ ሲነገረን የቆየው ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት የየጎሳ ጥምር አገዛዝ (ethnic federalism) ነው። በማንኛውም የፓለቲካ ችግር የዚህ አይነት የፓለቲካ ሳይንስ የሌለ መሆኑ ነው። ምን አይነት ቅጥፈት ነው ሂትለር እንዳስትማረው ሰወች ትልቅን ዉሸት ከአነስተኛ ውሸት ይልቅ በበለጠ በቶሎ ያምኑታል። ሰወች በተደጋጋሚ ሐሰት ሲነገራቸው በቶሎ ወይም ዘግየት ብለው ያምናሉ። እኛ ግን አናምነውም።

## ከፍተኛ ውሸታሞች ስለሆኑ ይዋሻሉ

ውሸታም ውሸታም ሱሪ በእሳት ላይ " liar, liar pants on fire" ወሽታሞችና ውሸት አዳባሪ ውሸታሞች አሉ ቢል ክሊንትን ሲናገር ማሩዋና (እፅ) አጭሼአለሁ፣ ነገር

ግን ወደ ውስጥ አልሳብኩትም፣ ባለቤቱ በቦዝኒያ ጉብኝቷ ከአውሮፕላን ስትወርድ ጠላትን ለማስውግድ  በሚችል የተጠመደ መሳሪያ ተከባ አቀባባል እንደተደረገላት ተናግራለች። ጆርጅ ቡሽና ቶኒ ቢለር በኢራቅ አለምን የሚያጠፋ መሳሪያ ነበር በማለት ማሉ። ቢልና ቶኒ መለስን ከአፍሪካ መሪዎች አዲሱ ግኝት ብለው ሰየሙት። መለስ ኢትዮጵያ የሕዝብ ሙብት ያላት አገር ነች። ሱማሊያን ግን ከአልካይዳ ጋር ትንከባለላለች ብሏል። ሁሉም የተረገሙ ዉሸታሞች ናቸዉ። በእኛ አመለካከት ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች ለምን እንደሚዋሹ ያስረዳናል። መለስን እውነተኛውን የፓለቲካ ጥራት ለማስረዳት እድሉ ቢሰጠውና ለመኖር ምን እንደሰራ ቢጠየቅ የቶሎስቶይን አባባል በመውሰድ ‘በስው ትከሻ ላይ ተፈናጥጬ ጉሮሮውን በማንቅ እንዲሸከመኝና ራሴንም ለእሱ ያዘንኩ በማስመሰል ሸክሙን ለማቅለል ከወገብ ላይ ሳልወርድ የምችለዉን ነገር ሁሉ ለማድረግ እመኛለሁ ብሎ እንደሚናገር ግልፅ ነው። ከላያችን ላይ ውረድ?